ECSOC

# የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
# ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ድ.ም/መን 122/15

ቀን/Date ሚያዝያ 05/2015 ዓ.ም

## መግለጫ

### በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ

*ሚያዝያ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ፡ አዲስ አበባ፦* የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በሃገራችን በሚስተዋሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ የሲቪል ማህበረሰቡን ድምጽ ሲያሰማ መቆየቱ ይታወሳል። በዚህም የሃገራችንን ሰላም እና ደህንነት የሚያውኩ ግጭቶች እና አለመግባባቶች ከሃይል አማራጭ ውጭ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ፤ የትጥቅ ግጭቶች ሁሉ ቆመው፤ ሁሉን አካታች ሰላማዊ እና ዘለቄታዊ መቋጫ እንዲፈለግላቸው ሲያሳስብ ቆይቷል።

ከሰሞኑም የክልሎችን ልዩ ሀይልን መልሶ ለማደራጀት ከተደረሰው ውሳኔ ጋር ተያይዞ እየተፈጠሩ ያሉ ሁኔታዎችን ምክር ቤቱ በአንክሮ ሲከታተል ቆይቷል። በተለይም በአማራ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰተው ግጭት በሰዎች ላይ የአካል ጉዳት እና የህይወት መጥፋት መድረሱን ተረድተናል። ህይወታቸው ካለፉ ሰዎች መካከል የካቶሊክ ሪሊፍ ሰርቪስ ግብረ ሰናይ ድርጅት ሁለት ሰራተኞች እንደሚገኙበት እንዲሁም በስራ ላይ በነበሩ የቀይ መስቀል ሰራተኞች ላይም ጉዳት የደረሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በሰብአዊ ድጋፍ ስራ ላይ በተሰማሩ ሰራተኞች እየደረሰ ያለው ተደጋጋሚ ጥቃት እና ህልፈተ ህይወት በእጅጉ ያሳዘነን ከመሆኑም በላይ መሰል ጥቃቶች በሰብአዊ እርዳታ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያከናውኑትን የሰብአዊ ድጋፍ ስራን በማስተጓጎል፤ የዕለት እርዳታ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ECSOC ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

☎ (251) 11 853 2005/8/9
Email: ECSOC22@gmail.com
URL:www.ecsoc.net
@ethiopian.cso_council
@Eth_CSO_Council
@ethiopian_cso_council
Ethiopian Civil Society Organizations Council
Location: Left flank, 3rd floor, Hibr Building of Hibret Bank, Addis Ababa Ethiopia

Scanned with CamScanner

የሚፈልጉ ዜጎች ተገቢው ድጋፍ በወቅቱ እንዳይደርሳቸው የሚያደርግ በመሆኑ ምክር ቤቱን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳስበዋል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጲያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በዜጎች እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እና ሰራተኞች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት እንዲቆም፣ ተገቢው ጥበቃም እንዲደረግ ጥሪ ያቀርባል፡፡

በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሀገራችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን፣ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና አለመግባባቶች ሁሉ በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የጀመረውን ሁለንተናዊ ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ለማረጋገጥ ይወዳል፡፡

***<u>ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት</u>***

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ሲሆን ህጋዊ ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ4400 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*

CS Scanned with CamScanner